# የሶስተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ

## ምዕራፍ አንድ ፡ ሙከራ ጥያቄ አንድ

I. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1. የተለያዩ ወረዳዎችን የያዘ የአስተዳደር እርከን ምን ይባላል ?

   ሀ) ቀበሌ ለ) ከተማ

   ሐ) ክፍለ ከተማ መ) ሰፈር

2. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስንት ክፍለ ከተሞች ይገኛሉ ?

   ሀ) 10 ለ) 8 ሐ) 12 መ)11

3. በአዲስ አበባ ሰሜናዊ ክፍል የሚገኙት ክፍለከተሞች የትኞቹ ናቸው ?

   ሀ)ጉለሌ እና የካ ለ)ቂርቆስ እና ልደታ

   ሐ) ኮልፌ ቀራኒዮ መ) ንፋስልክ ላፍቶ እና አቃቂ

4. ዋና ዋና መሰረታዊ አቅጣጫዎች ስንት ናቸው ?

   ሀ)3 ለ) 4 ሐ) 7 መ)6

5. ከሚከተሉት ውስጥ ከዋና ዋና መሰረታዊ አቅጣጫዎች የሆኑትን ምረጡ?

   ምሥራቅ ደቡብ ምዕራብ ሰሜን ደቡብ

   ምዕራብ ሰሜን ምስራቅ

6. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ አንፃራዊ መገኛ ትክክል ይሆነው የቱ ነው ?

   ሀ) አንድን ነገር ከአካባቢው ካሉ ታዋቂ ቦታዎችን ጋር በማነፃፀር የምናገኝበት ዘዴ ነው

   ለ) የኬክሮስን እና ኬንትሮስን በመጠቀም የአንድን ነገር ትክክለኛ ቦታ የምናገኝበት ዘዴ ነው

   ሐ) ህንፃዎች፣ ወንዞች፣ መንገዶች እና የመሳሰሉትን እንጠቀማለን

   መ) ሀ እና ሐ

LIVEWORKSHEETS

7. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ፍፁማዊ መገኛ ትክክለ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) አንድን ነገር ከአካባቢው ካሉ ታዋቂ ቦታዎችን ጋር በማነፃፀር የምናገኝበት ዘዴ ነው

ለ) የአንድን ነገር ትክክለኛ ቦታ ለማግኘት የኬክሮስን እና ኬንትሮስን መስመሮች ይጠቀማል

ሐ) የአንድን ነገር ትክክለኛ መገኛ ማወቅ ያስችለናል

መ) ለ እና ሐ

8. ከሚከተሉት ውስጥ በአዲስ አበባ ምዕራባዊ ክፍል የሚገኘው የቱ ነው ?

9. ከመነሻ ዋልታ በስተምስራቅ እና በስተ ምዕራብ በቋሚ መስመሮች መካከል ያለውን ርቀት የሚለካ መስመር ምን ይባላል ?

ሀ) ኬንትሮስ ለ) ኬክሮስ

ሐ) ሀ እና ለ መ) መልስ የለም

10.መሬትን ምስራቃዊ እና ም ዕራባዊ ንፍቀ ክበብ በማለት እኩል ቦታ የሚከፍል የሃሳብ መስመር ምን ይባላል ?

ሀ) ዜሮ ዲግሪ ኬንትሮስ ለ)ፕራይም ሜሪዲያን

ሐ) መነሻ ዋልታ መ) ሁሉም

11.የፕራይም ሜሪዲያን መስመርን መነሻ በማድረግ በስተ ምስራቅ ወይም በስተ ምዕራብ የኬንትሮስ መስመሮች ምን ያህል ዲግሪ ይለካሉ ?

ሀ) 120 ለ) 180

ሐ) 360 መ) 0

12.የፕራይም ሜሪዲያን መስመርን መነሻ በማድረግ የኬንትሮስ መስመሮች ባጠቃላይ ምን ያህል ዲግሪ ይለካሉ ?

ሀ) 120 ዲግሪ ለ) 180 ዲግሪ

ሐ) 360 ዲግሪ መ) 0 ዲግሪ

LIVEWORKSHEETS

13.በካርታ ላይ ተመሳሳይ ኬንትሮስ ያላቸውን ቦታዎች የሚያገናኝ የሃሳብ መስመር ምን ይባላል ?


ሀ) ቋሚ መስመር

ሐ) የምድር ወገብ

ለ) ኬንትሮስ

መ) ሀ እና ለ

14.ከምድር ወገብ ሰሜን እና ደቡብ በተጓዳኝ መስመሮች መካከል ያለውን ርቀት የሚለካ መስመር ምን ይባላል ?




15.የኬክሮስ መስመሮች ከምድር ወገብ ወደ ሰሜን እና ወደ ደቡብ በስንት ዲግሪ ይለካሉ ?

16.የኬክሮስ መስመሮች ከምድር ወገብ ወደ ሰሜን እና ወደ ደቡብ በአጠቃላይ በስንት ዲግሪ ይለካሉ ?

17.መሬትን ሰሜናዊ እና ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ በማለት የሚከፍለው የሃሳብ መስመር ማን ይባላል ?

ሀ) ዜሮ ዲግሪ ኬክሮስ

ለ) የምድር ወገብ

ሐ) መነሻ ዋልታ

መ) ሀ እና ለ

18.እርስ በእርሳቸው የማይቆራረጡ ተመሳሳይ ኬክሮስ ያላቸውን ቦታዎች የሚያገናኙ መስመሮች ምን ይባላሉ ?

ሀ) ተጓዳኝ መስመር

ለ) ኬንትሮስ

ሐ) ኬክሮስ

መ) መነሻ ዋልታ

LIVEWORKSHEETS

19.ሁሉም ተጓዳኝ መስመሮች ከየት ወድየት ይሰመራል ?

ሀ) ከሰሜን ወደ ደቡብ

ለ) ከምስራቅ ወደ ም ዕራብ

ሐ) ከምዕራብ ወደ ምስራ

መ) ለ እና ሐ

20.የምድር ወገብ ስንት ዲግሪ ላይ ይገኛል ?

ሀ) $180^0$

ለ) $0^0$

ሐ) $90^0$

መ) $360^0$

21.ከሚከተሉት ውስጥ የጎግል ካርታ መፈለጊያ ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ) የአንድን ቦታ ትክክለኛ መገኛ ለማወቅ ይረዳል፤

ለ) ተጠቃሚዎች የጓደኝነት ግ ንኙነት እንዲኖራቸው ይረዳል፤

ሐ) ለሚጠየቀው ጥያቄ በፍጥነት መልስ ይሰጣል፤

መ) መልስ የለም

II.የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሃሰት በማለት መልሱ

1. አራቱን መሰረታዊ አቅጣጫዎች በመጠቀም የአንድን ነገር ትክክለኛ መገኛ ማወቅ ይቻላል ፡፡
2. የተለያዩ ወረዳዎችን በስሩ የያዘ የአስተዳደር እርከን ክፍለ ከተማ ይባላል ፡፡
3. በአካክባቢው ካሉ ታዋቂ ቦታዎች ጋር በማነፃፀር  የአንድን ነገር መገኛ የምናመለክትበት ዘዴ ፍፁማዊ መገኛ ይባላል ፡፡
4. ኬክሮስ እና ኬንትሮስን በመጠቀም የአንድን ነገር መገኛ የምናመላክትበት ዘዴ ፍፁማዊ መገኛ ይባላል፡፡
5. መሬትን ምስራቃዊ እና ም ዕራባዊ ንፍቀ ክበብ በማለት የሚከፍለው የሃሳብ መስመር መነሻ ዋልታ ይባላል፡፡

LIVEWORKSHEETS

6. ከምድር ወገብ ሰሜን እና ደቡብ በተጓዳኝ መስመሮች መካከል ያለውን ርቀት የሚለካ የሃሳብ መስመር ኬክሮስ ይባላል ፡፡

7. የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞችን መገኛ ለማወቅ አራቱን መሰረታዊ አቅጣጫዎች በመጠቀም መግለጽ አይቻልም፡፡

8. ጉለሌ እና የካ ክፍለ ከተሞች የአዲስ አበባ ምስራቃዊ ክፍል የሚገኙ ናቸው ፡፡

9. አራዳ ፣ ልደታ፣ ቂርቆስ እና አዲስ ከተማ የማሃል አዲስ አበባ ክፍሎች ናቸው ፡፡

10. ንፋስ ስልክ ላፍቶ እና አቃቂ ቃሊቲ የአዲስ አበባ ደቢባዊ ክፍሎች ናቸው ፡፡

11. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ ክፍለከተሞች የራሳቸው የሆነ ፍፁማዊ መገኛ አላቸው ፡፡

12. የክፍለከተሞችን አንፃራዊ መገኛ ለማግኘት ኬክሮስ እና ኬንትሮስን እንጠቀማለን ፡፡

13. የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያን በመጠቀም የአንድን ቦት ትክክለኛ መገኛ ለማግኘት አይረዳም ፡፡

14. የክፍለከታማችንን አንፃራዊ መገኛ ለማወቅ በአካባቢው ያሉትን ክፍለከተሞችን ማወቅ ይኖርብናል፡፡

LIVEWORKSHEETS